የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ሠላሳኛ ዓመት ቁጥር ፲
አዲስ አበባ ታህሳስ ፩ ቀን ፪ሺ.፲፮ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

30th Year No. 10
ADDIS ABABA, 11th December , 2023

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ.፫፻/፪ሺ.፲፮

ለኢትዮጵያ ኤሌክትሪፊኬሽን ፕሮግራም ማስፈጸሚያ የሚውል ብድር ከዓለም አቀፍ የልማት ማህበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ……………………………………ገጽ ፲፭ሺ.፪፻፹፰

## Content

Proclamation No. 1300/2023

International Development Association Loan Agreement for financing Ethiopia Electrification Program Ratification Proclamation …………………....Page 15288

### አዋጅ ቁጥር ፩ሺ.፫፻/፪ሺ.፲፮

### በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

ለኢትዮጵያ ኤሌክትሪፊኬሽን ፕሮግራም ማስፈጸሚያ የሚውል አንድ መቶ ሰማንያ ስምንት ሚሊዮን ሁለት መቶ ሺ. ኤስ.ዲ.አር. (፩፻፹፰ ሚሊዮን ፪፻ሺ. ኤስ.ዲ.አር.) ብድር የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል ግንቦት ፲፬ ቀን ፪ሺ.፲፭ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

### PROCLAMATION NO. 1300/2023

### A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE INTERNATIONL DEVELOPMENT ASSOCIATION

**WHEREAS,** the Loan Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association stipulating that the International Development Association shall provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Loan an amount equivalent to One Hundred and Eighty-Eight Million Two Hundred Thousand Special Drawing Rights (SDR 188,200,000) for financing Ethiopia Electrification Program, was signed in Addis Ababa on 22nd Day of May, 2023;

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በ፫ኛ ዓመት የሥራ ዘመኑ ጥቅምት ፩ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም በአካሄደው ፩ኛ መደበኛ ስብሰባ ያጸደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

፩. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "ለኢትዮጵያ ኤሌክትሪፊኬሽን ፕሮግራም ማስፈጸሚያ የሚውል ብድር ከዓለም አቀፍ የልማት ማህበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻/፪ሺ፲፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. <u>የስምምነቱ መጽደቅ</u>

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል ግንቦት ፲፬ ቀን ፪ሺ፲፭ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመው የብድር ስምምነት ቁጥር 7294-ET በዚህ አዋጅ ጸድቋል፡፡

፫. <u>የገንዘብ ሚኒስቴር ሥልጣን</u>

የገንዘብ ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን አንድ መቶ ሰማንያ ስምንት ሚሊዮን ሁለት መቶ ሺ ኤስ.ዲ.አር. (፩፻፹፰ ሚሊዮን ፪፻ሺ ኤስ.ዲ.አር.) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

**WHEREAS**, the House of Peoples' Representatives of The Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said agreement at its 3rd year working period, 1st ordinary session held on 12th Day of October, 2023;

**NOW, THERFORE,** in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows.

**1. <u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as the "International Development Association Loan Agreement for financing Ethiopia Electrification Program Ratification Proclamation No. 1300/2023".

**2. <u>Ratification of the Agreement</u>**

The Loan Agreement Number 7294-ET signed in Addis Ababa on 22nd Day of May, 2023 between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association is hereby ratified.

**3. <u>Power of the Ministry of Finance</u>**

The Ministry of Finance is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan an amount equivalent to One Hundred and Eighty-Eight Million Two Hundred Thousand Special Drawing Rights (SDR 188,200,000) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

**፬. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ታህሳስ ፩ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም**

**ሣህለ ወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**4. <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall enter into force up on its publication in the Federal Negarit Gazettee.

**Done at Addis Ababa, On this 11th Day of December, 2023**

**SAHLE-WORK ZEWDIE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**